Customs Commission No.2

28 ሚያዚያ 2014

6-3/0163/14

የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>ለኮቪድ-19 መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የተፈቀዱ የህክምና ግብዓቶች ዝርዝር ላይ የተደረገ ማሻሻያን ይመለከታል</u>፡፡

እንደሚታወቀው ከገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/7/42 በቀን 18/07/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የኮቪድ-19 በሽታን ለመግታትና ለመቆጣጠር እንዲቻል በርካታ እቃዎች ከረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር እንዲገቡ በፈቀደው መሰረት በCPC 421 እየተመዘገቡ እንዲስተናገዱ መጋቢት 19 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር 4/0650/12 ማሳወቃችን ይታወሰል፡፡ ሆኖም የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/7/5371 በቀን 13/08/2014ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ቀድሞ በቁጥር ማኢ.30/7/42 በቀን 18/07/2012 ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆኖ እንዲገባ የተፈቀደው ተሽሮ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በተደረገው ዝርዝር መሰረት የኮቪድ-19 መከላከያና መቆጣጠሪያ የህክምና ግብዓቶች ዝርዝር የተተካ መሆኑን በመግለጽ፣ አፈጻጸሙን በተመለከተ ከጤና ሚኒስቴር ማረጋገጫ ሲቀርብ አገልግሎት እንዲሰጥ አሳስቧል፡፡

በመሆኑም ቀድሞ በቁጥር ማኢ.30/7/42 በቀን 18/07/2012 ለኮቪድ-19 መከላከያና መቆጣጠሪያ የህክምና ግብዓቶች የተፈቀደዉ የቀረጥና ታክስ ነጻ አገልግሎት የተሻረና በቁጥር ማኢ.30/7/5371 በቀን 13/08/2014ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተላለፈው ዝርዝር መሰረት ከቀረጥና ታክስ ነጻ አገልግሎቱ እንዲሰጥ እናሳስባለን፡፡

አተገባበሩን በተመለከተ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ አባሪ በተደረገው 1 ገጽ ዝርዝር መሰረት በታሪፍ ቁጥር የተለዩት የህክምና ግብዓቶች ብቻ በዕቃ መግለጫቸው መሠረት ስለመሆናቸው እየተረጋገጠና ከጤና ሚኒስቴር ማረጋገጫ እየቀረበባቸው ወደ አገር የሚገቡ መሆኑ ታውቆ በዝርዝሩ ላይ እቃዉን በተመለከተ በተጠቀሰው ታሪፍ ቁጥር እየተመደቡ አገልግሎት እንዲሰጥ እንዲደረግ፤ የታሪፍ ቁጥር 38220000 በታሪፍ ቁጥር 3822.1900 እና የታሪፍ ቁጥር 9027.8000 በታሪፍ ቁጥሮች 9027.8100ና 9027.8900 በRemark ላይ እንዲተኩ በታረመው መሰረት ሆኖ፤ **በአባሪው ላይ የታሪፍ ቁጥራቸው ያልተጠቀሱት ግብዓቶችን በተመለከተ ግን ከጤና ሚኒስቴር በዝርዝር ተለይተው እስከሚቀርቡ ድረስ ለጊዜው የቀረጥና ታክሱን ተመጣጣኝ ዋስትና**

እያሲያዙ አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳሰብን፣ የተደረገው ማሻሻያ ከ13/08/2014 ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን በ \\10.12.0.8 ሎካል ሼር አድራሻ ላይ Tariff Classification -Folder/ Tariff Policy and Classification-Folder/ከመስከረም 1.2014 ዓ.ም በኋላ የመጡ የታሪፍ ማሻሻያዎች-Folder/ኮቪድ-19-Folder/ ውስጥ ኮቪድ-19 ታሪፍ ማሻሻያ ሚያዝያ 18 2014 ዓ.ም በሚል የፋይል ስም የተቀመጠ መሆኑን እናሳቃለን፡፡

ከገንዘብ ሚኒስትር ከ13/08/2014 በተላለፈው ዝርዝር ውስጥ የታሪፍ ቁጥራቸው ሳይጠቀስ በጥቅል አገላለጽ የጠቀመጡትን ግብዓቶች በተመለከተ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጤና ሚኒስቴር በዝርዝር በታሪፍ ቁጥር በመለየት ለኮሚሽኑ እስከሚልክ ድረስ አገልግሎት ለመስጠት የምንቸገር መሆኑ ታውቆ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተቻለ ፍጥነት ዝርዝራቸውን ከነታሪፍ ቁጥራቸው በማዘገጀት ለኮሚሽናችን እንዲያሳውቅ በዚህ ደብዳቤ ግልባጭ እንዲያውቀው ተደርጓል፡፡

ከሠላምታ ጋር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission No.2

ግልባጭ፡-

- ለጤና ሚኒስቴር
- ለገንዘብ ሚኒስቴር

  አዲስ አበባ

ግልባጭ፡-

- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ስራአመራር ስርአት ፕሮጀክት ጽ/ቤት
- ለንግድ ዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ፖሊሲ ጥናትና ትንተና ቡድን
- ለታሪፍ ምደባ አሰራርና ድጋፍ ቡድን

  ጉምሩክ ኮሚሽን

